www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7፤ የፍትሕ፤የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

ግንቦት 21 2000 ዓም ቁጥር

---

## ሕጋዊ» ዘረፋ፤ የሽፍቶች ካፒታሊዝም በኢትዮጵያ።

ብርሃኑ ነጋ

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያችን የሚሰማው ኢኮኖሚ ነክ ወሬ በጣም እርስ በእርሱ የሚጋጭ ስለሚመስል ጉዳዩን ለሚከታተል ሰሚ እጅግ ግራ ቢያጋባው የሚያስገርም አይደለም። የኢትዮጵያ መንግስት በታሪክ ታይቶ ስለማይታወቀው ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት በየጊዜው የሚደሰኩረው ፕሮፓጋንዳ፤ ለጉብኝት ወደ አዲስ አበባ ሄደው የሚመጡ ኢትዮጵያውያን ስለአዲስ አበባ አስደናቂ እድገትና ስለ ፎቆችና መንገዶች መሰራት የሚያወሩት ወሬ፤ በቅርቡ የአለም የገንዘብ ድርጅት ስለ ኢትዮጵያ ያወጣው አወንታዊ የኢኮኖሚ ዘገባና ተመሳሳይ አወንታዊ ዘገባዎች በአንድ በኩልና፤በእለት ተቀን ከነዋሪው ህዝብ ከምንሰማው «እንዲህ አይነት አስከፊ ኑሮ በታሪካችን አይተን አናውቅም » ምሬት፤ በአገሪቱ ረሀብ ስለመግባቱ በምስል እየተደገፈ ከሚቀርበው ዜና ጋር ፍፁም የሚጣጣም አይደለም። በመንግስት በኩል የሚወራውን ወሬ እንደ ዘወትር ውሸታቸው አቃለን ብናልፈው እንኳዋን ከሌሎቹ የሚሰማው ወሬን ዝም ብለን ልናልፈው አንችልም። ቢያንስ ነገሩን ለመረዳት መጣር፤ ተረድቶም ላይ ላዩን ከሚታየው ውስጥ ገብቶ የሚሆነውን ነገር ማወቅ የአመለካከት ጥራት ስለሚሰጠን ለዴሞክራሲ ትግሉ እጅግ ጠቃሚ ነው። በዚህ ላይ የግንቦት 7 ድምፅ አትኩረት ሰጥቶ ወደፊት ተከታታይ ፅኑፎች ያስነብበናል በዬ እጠብቃለሁ። በዚህ አጭር ፅኑፍ የአገሪቱን ኢኮኖሚ አጠቃላይ ገፅታ ወይንም ደግሞ እነኝህን የተጣረሱ መረጃዎች ሙሉ ለሙሉ ለመፍታት የሚያስችል ትንተና ለመስጠት አልታሰበም፤ ቢታሰብም የሚቻል አይደለም። የፅሁፉ አላማ በጣም ጠባብ ግን በእኔ እምነት አስፈላጊ ነገር ነው። በኢኮኖሚው ዙሪያ የሚካሄደውንና በጣም ዘላቂ የሆነ እንድምታ ያለውን አንድ ክስተት ብቻ በመመልከት የነገሩን አደገኛነት ለማሳየትና የህዝቡንና ለዴሞክራሲ የሚታገለውን ሀይል ቀልብ ወደዚያ እንዲያነጣጥር ለማመላከት ብቻ ነው።

በመጀመሪያ ብዙ በማያጣሉት ሶስት እውነታዎች ላይ እናተኩር።

1) በእርግጥም በአዲስ አበባ ብዙ ህንፃዎች ይሰራሉ፤ ህንፃዎቹም እንደ ከዚህ በፊቱ በቁጥቁጥና ብዙ ገንዘብ ላለማውጣት በመጠንቀቅ የሚሰሩ ሳይሆኑ በተወሰነ ደረጃ ዘመናዊ የሆኑ፤ ለማሳመር የሚወጣ ወጪ ላይ ቸር የሆኑ ትላልቅ ህንፃዎች ናቸው። ይህም ማለት ባለቤቶቹ ወይንም በጣም ብዙ ብር ያላቸው ናቸው፤ አለያም ገንዘብ በቀላሉ የሚያገኙበት ምንጭ አላቸው። በከተማው የሚሰሩ መንገዶች ጉዳይ ብዙም የተወሳሰበ ነገር አይደለም። በመንግስት ወጪ፤ መንግስት አንድም ከውጭ መንግስታት አለያም ህዝቡ ካስቀመጠው ገንዘብ በመበደር የሚሰሩ ናቸው።

2) በአጠቃላይ በአገሪቱ በተለይ ደግሞ በከተሞች ከዚህ በፊት በአገሪቱ ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት አለ። ይህ የዋጋ ግሽበት በአነስተኛው ወደ 30 ከመቶ፤ ግን እንደ ነዋሪው ስሌት ከዚያም በብዙ እጥፍ (አንዳንድ ጊዜ በየሳምንቱ የሚጨምር) የበለጠ የዋጋ ጭማሪ በሁሉም አይነት ሸቀጦችና ግልጋሎቶች ላይ እየታየ ነው። ይህ የዋጋ

ግሽበት የፈጠረው የኑሮ ውድነት እንደ ኢትዮጵያ ያለ ድሀ አገር ላይ በብዙሀኑ ህዝብ ላይ የሚፈጥረው የኑሮ ቀውስ እጅግ አስከፊ ነው:: በብዙ የአገሪቱ ከተሞች ነዋሪው ህዝብ በእውነት እየተራበ መሆኑ የሚገርም አይደለም::

3) በጣም በሚገርም ሁኔታና ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መጠን ሙስና ተስፋፍቶአል:: የሙስናው ደረጃ ከከፍተኛ ባለስልጣኖች አልፎ መሀከለኛ የፖለቲካና የቢሮክራሲ ካድሬ ጋር ደርሶአል:: ከዚህ ውስጥ ምንም በመንግስት ስራ ላይ ያልተሰማሩ፣ ከዚህ ቀደም የፖለቲካ ወይንም ወታደራዊ ካድሬ የነበሩ ሰዎች በ«ጉዳይ አስፈፃሚነት» ስም በቀጥታ በንግድ ውስጥ የተሰማራውን ጊዜኛ ከበርቴ በተለያየ ደረጃ ከሚገኙ የመንግስት ባለስልጣናት ጋር የሚያገናኘውና (ጠቀም ያለ ኮሚሽኑን በልቶ) የሙስና ቅብብሉን የሚያሳልጥ አዲስ አቀባባይ ከበርቴ ተፈጥሮአል::

እነኝህ ሶስት እውነታዎች የተለያዩ ይምሰሉ እንጂ በጣም የተገናኙ ናቸው:: **በተግባር እየሆነ ያለውም ምናልባት ከየካቲት 66 ዓ.ም የደርግ ንብረት ውርስ ወዲህ (የመሬት አዋጅ፣ የፋብሪካዎች ማገርና የከተማ ቤቶችን መውረስ) በጣም ከፍተኛው የንብረት ዝውውር በአገራችን አሁን እየተካሄደ ነው:: ይህ እንዴት እንደሆነ በአጭሩ ከማሳየቱ በፊት ግን በሁለቱ የንብረት ዝውውሮች መሀከል ያለውን አንድ መሰረታዊ ልዩነት ላስቀምጥ:: በ66 አብዮት ጊዜ የተደረገው የንብረት ዝውውር በገጠር ከመሬት ባለሀብቱ ተወስዶ መሬት ወደሌለው የቀድሞ ጭሰኛና መሬት የሌለው ድሀ ገበሬ፣ በከተማ ቦታና መሬት ውርስ ከአከራዮች ወደ ተከራዮችና የመንግስት ባለሙዋሎች፣ በፋብሪካዎች ደግሞ ከከበርቴው ወደ መንግስት በአጠቃላይ ግን በፊት ለፊትና በአዋጅ፣ ከጥቂት ባለሀብቶች ወደ ብዙሀን ድሆች የተደረገ የንብረት ዝውውር ነው:: የአሁኑ የንብረት ዝውውር በአዋጅና በፊትለፊት የሚደረግ አይደለም:: ከዚያም በላይ የንብረት ዝውውሩ የሚደረገው ከድሀው፣ የተወሰነ ገቢ ካለው (ለምሳሌ ጡረተኛ) ወይንም ተራ ደሞዝተኛ፣ ከአነስተኛው ነጋዴና ገበሬ፣ ተወስዶ ንብረት ወይንም ትላልቅ ንግድ ወዳለው ሀብታም፣ ከዚህም ውስጥ በተለይ የመንግስት ድጋፍ ወዳለው የተወሰነ የሀብታም ክፍል ወይንም ሆን ተብሎ ወደሚፈጠር አዲስ የሀብታም መደብ መሆኑ ነው:: በሚገርም ሁኔታና ፍጥነት አጠቃላይ የአገሪቱ ሀብት እየተስፋፋ ሳይሆን ባለው ሀብት አዲስ የኢኮኖሚ ገዢ መደብ እየተፈጠረ መሆኑ ነው:: የንብረት ሽግግሩ ባጠቃላይ ከብዙሀኑ ወደ አናሳዎች ነው:: ስለዚህም ባለውና በሌለው መሀከል ያለው ልዩነት ሆን ተብሎ በሚያስፈራ ሁኔታ እየሰፋ ነው::** ይህ አዲስ ሁኔታ እንዴት እየተፈጠረ እንደሆነ በአጭሩና በቀላሉ ለዚሁ ተብሎ በግርድፉ በተዘጋጀ ምሳሌ ላስረዳ:: ምሳሌው ላይ ያለው ሂሳብ አጠቃላይ ቅኝቱን ለማሳየት በሚልና ስሌቱ እንዳይንዛዛ በጥቅሉ ነው የቀረበው::

ማንም እንደሚያውቀው አብዛኛውና በተለይ በትላልቅ የንግድና የኢንቬስትመንት ስራ ላይ የሚደረግ ወጪ ከባንክ በሚገኝ ብድር ነው:: በኢትዮጵያ ለሚደረግ ከፍተኛ ንግድ ወይንም ኢንቬስትመንት ባለሀብቱ 30 በመቶ ማቅረብ ከቻለ ባንኮች 70 ከመቶውን በብድር መልክ ይሰጣሉ:: መንግስትም ለሚያደርገው ማናቸውም እንቅስቃሴ ብር ሲያንሰው ከብሄራዊ ባንክ ተበድሮ ነው የሚሰራው:: ምንም እንኩዋን ባለሀብቶች ቢያንስ 30 ከመቶውን ማስቀመጥ ቢጠበቅባቸውም እሱንም ከኪሳቸው ለማውጣት ካልፈለጉ በሙስና (በጉዳይ አስፈፃሚዎች በኩል?) ከዚያም ያነሰ አውጥተው ብድሩን ያገኛሉ:: ስለዚህ አንድን የኢንቬስትመንት እንቅስቃሴ ለመጀመር ብዙ የግል ገንዘብ አያስፈልግም በተለይ ጥሩ ግንኙ ነቶች ከሉ:: በማስያዣነትም የሚያዘው ብዙውን ጊዜ ይኸው የሚሰራው ንብረት ነው:: ባንኩ የመንግስት ከሆነ ደግሞ የሚያስፈልገው ግንኙነት ከመንግስት ባለስልጣኖች ጋር ነው ማለት ነው::

ባንኮች በበኩላቸው እንዴት እንደሚሰሩና ትርፍ እንደሚያገኙ ይታወቃል:: ተራ ሰዎች ያላቸውን ገንዘብ በኪሳቸው ወይንም በፍራሻቸው ውስጥ ከሚያስቀምጡ ብራቸውን አነስተኛም ቢሆን ወለድ በሚያስገኝ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ያስቀምጣሉ:: ለዚህም ባንኩ የተቀማጭ ሂሳብ ወለድ (አሁን ላለፉት ብዙ አመታት 3 ከመቶ ነው) ይከፍላቸዋል:: ይህን ከህዝቡ የሰበሰበውን ገንዘብ ለተበዳሪዎች በከፍተኛ ወለድ ያበድራል (ይህ ደግሞ ወደ 8 ከመቶ አካባቢ ነው):: የባንኩ ትርፍ በሁለቱ መሀከል ካለው ልዩነት ላይ ወጪዎቹን ቀንሶ (የሰራተኛ ደሞዝ፣ የቤት ኪራይ...ወዘተ) የሚያገኘው ነው ማለት ነው:: ለምሳሌ አስቀማጮች በሙሉ አንድ ቢልዮን ብር ቢያስቀምጡና ከዚህ ውስጥ 800 ሚሊዮኑን ባንኮቹ ለደንበኛ ተበዳሪዎቹ ቢያበድሩ (ሁሉንም ሊያበድሩ አይችሉም የተወሰነውን አስቀማጮቹ ስለሚያወጡት) ባንኮቹ ለአስቀማጮች 30 ሚሊዮን በወለድ መልክ ይከፍላሉ:: ከተበዳሪዎቹ ደግሞ 64 ሚሊዮን ብር ይሰበስባሉ:: ከሁለቱ ልዩነት ከሚያገኙት 34 ሚሊዮን ብር

ውስጥ ወጪአቸውን ችለው የሚተርፈው ትርፋቸው ነው ማለት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ አስቀማጩም፣ ተበዳሪውም፣ አበዳሪ ባንኩም በተለያየ ደረጃ ይሁን እንጂ ሁሉም ይጠቀማሉ፡፡

ይህ ምሳሌ ግን አሳሳች ነው፡፡ ጊዜንና በጊዜ ውስጥ የሚፈጠረውን የብር የመግዛት አቅም ከግምት አያስገባም፡፡ አንድ አስቀማጭ አንድ መቶ ብር ባንክ ሲያስገባ በአመቱ መቶ ብሩ 103 ብር ይሆንልኛል ብሎ አስቦ ነው፡፡ አንድ ተበዳሪም በ8 በመቶ ወለድ ሲበደር የተበደረውን 100 ብር ሰርቶበትና አትርፎበት ከአመት በሁዋላ 108 ብር አድርጎ ለመመለስ ቃል ገብቶ ነው፡፡ ምንም የዋጋ ግሽበት በሌለበት ሁኔታ የዛሬ አንድ ብር ወጋ ከአመት በሁዋላም የመግዛት አቅሙ ያው አንድ ብር ነው ማለት ነው፡፡ የዋጋ ግሽበት ደግሞ የሚቀይረው ይህንን የብር የመግዛት አቅም ነው፡፡ ለምሳሌ የዋጋ ግሽበት በአመት አስር በመቶ ቢሆን ያ አንድ መቶ ብር በባንክ ያስቀመጠው ሰው ከአመት በሁዋላ በጥሬው የሚያገኘው 103 ብር የመግዛት አቅሙ 92 ብር ከሰባ ሳንቲም ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡ አስቀማጩ ሰውዬ ከራሱ ገንዘብ ላይ 7 ብር ከሰላሳ ሳንቲም ከስሮአል ማለት ነው፡፡ በአንፃሩ ተበዳሪው ለተበደረው 100 ብር ከአመት በሁዋላ የሚከፍለው 108 ብር የመግዛት አቅሙ ከዛሬ አንፃር ሲመዘን 97 ብር ከ 20 ሳንቲም ብቻ ነው፡፡ ማለትም ይህ ተበዳሪ ከባንክ በመበደሩ ባንኩ በነፃ 2 ብር ከ 80 ሳንቲም ከፍሎታል ማለት ነው፡፡ በእርግጥ ባንኩ ከራሱ ገንዘብ አይደለም የከፈለው፡፡ ከዚያ ምስኪን 100 ብር እጠቀማለሁ ብሎ ካስቀመጠው ድሀ ነው፡፡ ስለዚህ ዋና ተጠቃሚው ተበዳሪው ሲሆን ዋና ተጎጂው ደግሞ አስቀማጩ ናቸው ማለት ነው፡፡ ከአስቀማጩ ወደ ተበዳሪው ንብረት እየተዘዋወረ ነው ማለት ነው፡፡ የገንዘቡ መጠን በበዛ ቁጥር ደግሞ የተበዳሪው ጥቅም በዚያው ልክ እየጨመረ ይሄዳል ማለት ነው፡፡ ከአስቀማጩና ከተበዳሪው ውጭ ያለው ሌላው ከእጅ ወደ አፍ የሚኖረው ህዝብ ደግሞ ከአስቀማጩም በላይ በኑሮ ውድነት እየተለበለቡና እጅግ እየደኸዩ ይሄዳሉ፡፡

ይህንን ንድፈሀሳባዊ ስሌት በጭንቅላታችን ይዘን ከእውነት ጋር የሚቀራረብ አንድ ምሳሌ በመስጠት እንዴት የንብረት ዝውውር እየተደረገ እንደሆነ በአጭሩ እንመልከት፡፡ አንድ ባለጊዜ የመንግስት ባለስልጣን ዘመድ ወይም ጉዋደኛ ወይም የሚስጥር የንግድ ሸሪክ ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሰዎች ጋር ተመሳጥሮ አንድ ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ በሊዝ ይገዛል፡፡ የሊዙ ዋጋ አንድ ሚሊዮን ብር ቢሆን የሚከፍለው 10 በመቶ ክፍያ አንድ መቶ ሺህ ብር ይሆናል፡፡ ቀሪውን ምንም ዋጋ በሌለው ወረቀት በሀያ አመት ውስጥ ይከፍለዋል፡፡ የመጀመሪያውን ክፍያ በቀላሉ ተበድሮም ቢሆን ይከፍላል፡፡ በዚህ መሬት ላይ በጣም ዘመናዊ የሆነ 80 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ህንፃ ለመስራት ይወስንና ለባንክ ማመልከቻ ያስገባል፡፡ ያስገባው የኢንቬስትመንት ጥናት እንደሚያሳየው (እውነት ነው ብለን እንውሰደውና) ህንፃው ሲከራይ በወር አንድ ሚሊዮን ብር ወይንም በአመት 30 ሚሊዮን ብር በሚከፈልበት ጊዜ የብር ዋጋ እንደሚያስገባ ያሳያል ስለዚህም ብድሩን መክፈል ይችላል፡፡ ይህ «ልማታዊ ባለሀብት» መበረታታት እንዳለበት ከአንድ የመንግስት ባለስልጣን ወይንም በሱ የተወከለ «ጉዳይ አስፈፃሚ» የሚነገራቸው የባንክ ባለስልጣኖች ለራሳቸው የሚቀበሉትን ተቀብለው ብድሩን ባለቤቱ ባስገመተው ከፍተኛ ግምት (ለምሳሌ 150 ሚሊዮን ብር) መሰረት ያፀድቃሉ፡፡ ባለቤቱም ብድሩ እንደተፈቀደለት ከተነገረው በሁዋላ ገንዘቡ ከመለቀቁ በፊት የህንፃው 30 ከመቶ ወጪ የሚሆን ማውጣቱን እንዲያሳይ ይነገረውና ስራ ይጀምራል፡፡ ይህንን ትንሽ አራጣም ተበድሮ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ወይንም ብዙ ጊዜ እንደሚደረገው ትንሽ እንቅስቃሴ ካሳየ በሁዋላ ለባንኩ መሀንዲሶች ትንሽ ጉቦ ሰጥቶ የተጀመረው ሕንፃ 30 በመቶ ወጪ እንደወጣበት ይመሰክሩና የብድሩ ገንዘብ ይለቀቅለታል፡፡ ከተለቀቀለት ገንዘብ 80 ሚሊዮኑን ህንፃውን ለሚሰራው ለህንፃ ተቋዋራጭ ቢሰጠውና ከሚተርፈው 70 ሚሊዮን ውስጥ 50 ሚሊዮኑን ለመሬት ሊዝና ህንፃውን ለማስጀመር ለተበደራቸው አራጣ አበዳሪዎች ቢሰጥ በኪሱ ለመዝናኛ ወይንም ባለ መዋኛ የመኖሪያ ቤቱን ለመስራት በቂ ገንዘብ ይተርፈዋል ማለት ነው፡፡ ዋና የንብረት ዝውውር ታሪኩና የዝርፊያው አይነት ያለው ግን እዚያ ላይ አይደለም፡፡ የዋጋ ግሽበቱን እዚህ ጨዋታ ውስጥ ስናስገባው ነው መጠነ ሰፊ የንብረት ዝውውር እየተካሄደ መሆኑን የምናየው፡፡

በባንክ አሰራር መሰረት ይህ ሰው ቢያንስ ለሁለት አመት ህንጻው እስከሚያልቅና እስከሚከራይ ብድሩን ከመክፈል እረፍት ያገኛል፡፡ የሁለቱ አመት ወለድ በዋናው ብድር ላይ ተደምሮ (ወደ 24 ሚሊዮን ብር) ከሁለት አመት በሁዋላ የብድሩ አጠቃላይ መጠን በቀላል ስሌት ወደ 174 ሚሊዮን ብር ያድጋል፡፡ ብድሩ በአስር አመት ማለቅ ያለበት ቢሆን የመጀመሪያ ክፍያውን በሚከፍልበት በሶስተኛው አመት ላይ ከተከራዮቹ የሰበሰበውን በወር አንድ ሚሊዮን ብር ይከፍላል፡፡ የዚህ ሰውዬ

የመጀመሪያው የ150 ሚሊዮን ብር ብድር በአመቱ አሁን ባለው አነስተኛው ወደ 30 በመቶ በሚጠጋው የዋጋ ግሽበት ምክንያት ወደ 105 ሚሊዮን ብር ዝቅ ብሎአል። በሁለተኛው አመት ክፍያውን ሲጀምር ወለዱን ጨምሮ ያለበት 174 ሚሊዮን ብር ከ60 ከመቶ በላይ ቀንሶ ወደ 70 ሚሊዮን ብር ብቻ ይሆናል ማለት ነው። ይህ ሰውዬ እውነተኛ ብር ተበደሮ በያመቱ ዋጋውን ያጣ ወረቀት ነው ማለት ነው የሚከፍለው። በአንፃሩ በየአመቱ ከሚያገኘው (ከባንክ ክፍያ ከሚተርፈው) ገቢ በተጨማሪ የብድር ጊዜው ከአስር አመት በሁዋላ ሲያልቅ ምንም ዋጋውን የማያጣ ምናልባትም እየጨመረ የሚሄድ በመቶ ሚሊዮኖች የሚገመት ንብረት ባለቤት ይሆናል ማለት ነው። ይህን ንብረት ከየት አመጣው? መቼም ሰርቶ አይደለም። ካፒታሉን አውጥቶ አይደለም። እቆጥባለሁ ብሎ ገንዘቡን ባንክ ካስገባ ደሞዝተኛ፣ ከባንክ መበደር የማይችል የሸጠውን ባንክ ከሚያስቀምጥ አነስተኛ ነጋዴ፣ ከጡረተኛ...ወዘተ። እነኝህ ሁሉ ሰዎች ላባቸውን አንጠፍጥፈው የሰሩበትን ገንዘብ ዋጋውን እያጣ ነው በስውር እየተዘረፉ ያሉት። ይህ ግልፅ ዘረፋ በትክክለኛ መንገድ በሚሰራ የከበርቴ ስርአት ሊፈፀም አይችልም። ማንኛውም የኢኮኖሚ ባለሙያ እንደሚያውቀው እውነተኛው የባንክ ወለድ የባንኮች የማበደሪያ ወለድ ከዋጋ ግሽበት መጠን ጋር ተቀንሶ የሚገኘው ወለድ ነው። አሁን ኢትዮጵያ ባለው የማበደሪያ መጠንና የዋጋ ግሽበት መጠን መሰረት እውነተኛው የማበደሪያ ወለድ ከዜሮ በታች ከ22 በመቶ በታች ነው። ይህም ማለት አንድ ከባንክ ብድር ለማግኘት የቻለ ሰው ከባንክ ለሚበደረው ለእያንዳንዱ ብር እሱ ወለድ እየከፈለ ሳይሆን ባንኩ 22 ከመቶ ወለድ ይከፍለዋል ማለት ነው። በሌላ አነጋገር የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እውነተኛውን የካፒታሊስት ህግ የሚከተል ቢሆን በአሁኑ ጊዜ የሚኖረው የባንክ የማበደሪያ ወለድ ቢያንስ 30 ከመቶ መሆን ነበረበት ማለት ነው። ይህ ከሆነ ግን እነኝህ ህንፃ የሚሰሩት ባለሀብቶች ሊሰሩ ያዳግታቸዋል። እድገት የሚመስለው ነገርም ለማስመሰል እንኩዋን እንዳይቻል ባለበት ይቆማል። አሁን ባለው ሁኔታ ግን በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ይመታል። አቶ መለስ እድገት አመጣሁ ብለው መፎከርና ስለዚህም ስለ መብት፣ ስለዴሞክራሲ አታውሩ የሚለውን ደፋርና አይን ቀርጥፎ የበላ የፍፁም ንቀት ቱልቱላ ለመንፋት ያስችላቸዋል፣ አብረውም አጋሮቻቸውን ከባዶ ተነስተው የጠገቡ ዲታዎች ያደርጉዋቸዋል።

በዚህ አይነት ድምሩ ዜሮ የሆነ የንብረት ዝውውር ሁሉም ሰው ሊጠቀም አይችልም። ሁሉም ሰው ልበደር ብሎ ባንክ ቢሄድ ለዚያ ሁሉ የሚሆን ገንዘብ የለም። ስለዚህም የግድ ጥቂት ባለጊዜዎች ብቻ ናቸው ሊጠቀሙ የሚችሉት። ለዚህም ነው ብድር ለተወሰኑትና ጥሩ ንክኪ ላላቸው ብቻ የሚታደለው። የዚሕ አይነት ጥቂት አዳዲስ ሚሊየነሮች ከብዙሀኑ ህዝብ ኪስ እየወሰዱ ነው እየበለፀጉ ያሉት። የእነኝህን አይነት ዘራፊዎች ህንፃዎች እያሳዩ ነው እድገት መጣ የሚሉን። በእርግጥ ከመንግስት ጋር ሳይመሳጠሩ የሚሰሩ የሉም ማለት አይደለም። ነገር ግን የመንግስት ባለስልጣኖችና ቡችላዎቻቸውን ለመጥቀም የተፈጠረው ይህ ስርአት እነሱንም (ከባንክ መበደር እስከቻሉ ድረስ) በሰፊው እየጠቀማቸው መሆኑን መርሳት የለብንም። ለዚህም ሊሆን ይችላል እነኝህም ሰዎች መንግስትን ፊት ለፊት ለመኮነን ትንሽ የሚቸገሩት። መንግስት ከህዝቡ እየተበደረ የሚሰራው መንገድም ልክ እንደዚሁ ከአስቀማጬ ህዝብ የተዘረፈ ነው። በ30 ከመቶ የዋጋ ግሽበት መንግስት ከህዝቡ ለሚበደረው እያንዳንዱ ብር የሚከፍለው 70 ሳንቲም ብቻ ነው ማለት ነው። ለዚህም ነው መንግስት በጣም እየተበደረ የዋጋ ግሽበቱን ከቁጥጥር ውጪ እንዲወጣ ያደረገው። እነሱ ኬክ እስከበሉ ድረስ ሌላው የሚበላው ቢያጣ ደንታ የማይሰጣቸው ጭራቅ አዲስ ከበርቴዎች ነው እየተፈጠሩ ያሉት። የዚህ የዋጋ ግሽበት በሽታ ብዙ እንድምታ ነው ያለው። ከላይ ያቀረብኩት አነስተኛ ምሳሌ ግን ከንብረት ዝውውር ጋር በተያያዘ ላሳይ የፈለግሁትን ነጥብ ያሳየ ይመስለኛል።

በዚህ መልክ ከድሀውና ከመሀከለኛ ገቢ ካለው ደሞዝተኛ (የመንግስት ሰራተኞች፣ ወታደሮች፣ አስተማሪዎች፣ገበሬዎች፣ ሌሎች ሰራተኞችና ጡረተኞች) እየተመዘበረ ጥቂት ሰዎችን ሀብታም የሚያደርግ ሂደት፣ እየፈጠረ ያለው ሰፊ ልዩነት ምን የፖለቲካ እንድምታ አለው? አዲሶቹ የገዢ መደቦች ይህን እንዴት እያሰሉት ነው?

የዚህ ፖለቲካዊ እንድምታ እንዲገባን እነመለስ ቀደም ብለው ሲነግሩን ወደነበረው ማርክሳዊ ትንተና ይመልሰናል። ፖለቲካ የአንድ አገር ኢኮኖሚ ነፀብራቅ ነው፣ ኢኮኖሚውን የተቆጣጠረ ነው ለዘላቂው ፖለቲካውን የሚቆጣጠረው። አሁን ባለው የአለም ሁኔታ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ስርአት የከበርቴ ስርአት ከመሆን በቀር ምርጫ ስለሌለው ፖለቲካውን የሚቆጣጠረው የከበርቴው ክፍል ነው የሚሆነው። ስለዚህ እኛና የእኛ ደጋፊዎችን በሙሉ በአጭር ጊዜ ከበርቴ ስናደርግ ብቻ ነው በፖለቲካው የበላይነታችንን ይዘን መቀጠል የምንችለው። ይህን ሀብት በአስቸኳዋይ ለማካበት ያለን ብቸኛ አማራጭ ደግሞ

የፖለቲካ ስልጣኑን እንደዚህ እንደአሁኑ ሙሉ በሙሉ በምንቆጣጠርበት ሰአት እንዲህ አይነቱን ከፍተኛ የንብረት ዝውውር ማድረግ ስንችል ነው ከሚል በጣም አደገኛና መሰሪ ትንተና የመጣ፤ ታስቦበት የሚሰራ ስራ ይመስላል። በርግጥ አስበውበት ሆነም አልሆነም ግን ውጤቱ አንድ ነው። በአስቸኳዋይ ልናስቆመው ካልቻልን (ልናስቆመው የምንችለው ደግሞ በጉልበት የያዙትን የፖለቲካ ስልጣን መንጭቀን ማውጣት ስንችል ብቻ ነው) አገራችን ከምንጊዜውም በላይ ጥቂት በስራቸው ሳይሆን በስልጣናቸውና ከባለስልጣኖች ጋር በመሞዳሞድ ከፍተኛ ንብረት ያካበቱ የሸፍታ ከበርቴዎችና ከነሱ ፍርፋሪ የሚለቅሙ ህሊናቸውን የሸጡ ሆዳሞች እየተንደላቀቁ ፤ ይህን ምቾታቸውን ለመከላከል ደግሞ ህዝቡን እየረገጡና እየገደሉ፤ የሚኖሩባት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሆዳቸውን እያከኩ፤ የሚላስ የሚቀመስ አጥተው ከመቃብር በላይ ከኑሮ በታች የሆነ የምሬት ኑሮ ብዙሀኑ የሚኖርባት፤ ብዙሀኑም ለችግሩ እግዚአብሄርን እያማረረ የሚኖርባት አገር እንድትሆን ነው እያዘጋጁዋት ያለው።

ይህ የነሱ ምኞት ግን ሙሉ ለሙሉ ይሳካል ማለት አይደለም። በዚህ ሁኔታ የተማረረው ብዙሀን ምሬቱ አፎቱን ሞልቶ ሲፈስና ሞትን የማይፈራበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ይህንን የእነሱን የእድገት ምልክት የሆኑ ፎቆች ድምጥማጣቸውን ሊያጠፋ፤ ትንሽ ብር ያለውን ሁሉ እንደ ደመኛ ጠላቱ የሚያይበት ብሎም ካላጠፋሁ የሚልበት ፍፁም ያልተረጋጋና የአገሪቱን አብሮ መኖር የሚፈታተን ሁኔታ ሊፈጠር የሚችልበት እድል የዚያኑ ያክል መሆኑን ከዚህ ድሀ በዘረፉት ሀብት የሚበሉት ጥሬ ስጋና የሚጠጡት ውስኪ ጭንቅላታቸውን ፍፁም ካልጋረዳቸው፤ እነሱም ሳይገነዘቡት አይቀሩም። ለዚህም ይሆናል ብልጥ ነን ብለው የሚያምኑትና ይህ ነገር እንደማይዘልቅ የተረዱት ከዘረፉት ሀብት ገሚሱን በጊዜ ወደ ውጪ አገር የሚያሸሹት።

በአንፃሩ ለአገሪቱ በጎ የሚያስቡ ሀይሎች እንዲህ አይነት አደገኛ ሁኔታ እስከሚፈጠር ዝም ብለው የሚያዩበት ህሊና ሊኖራቸው አይገባም። ይህ የተከመረ ችግር በቀላሉ ሊመለስ የማይችልበት ደረጃ ከመድረሱ በፊት ትግላቸውን አስተባብረው፤ የእነኝህን ሀፍረተ ቢስ ሌቦች የስልጣን እድሜ ማሳጠር አለባቸው። በዚህ ነውረኛ መንግስት ምትክ የሚቁዋቁዋመው መንግስት በእውነትም ዴሞክራሲያዊ፤ በህዝብ ፈቃድና ይሁንታ ብቻ የሚያስተዳድር፤ ተጠሪነቱም ለመረጠው ህዝብ ብቻ የሆነ መንግስት እንደሆነ ህዝቡ ካወቀና ይህንንም ለማምጣት የሚደረገው ትግል የሚከተለውን የትግል አቅጣጫ ለህዝቡ በደንብ ካመላከተ፤ ያልተደራጀና በግብታዊነት የሚመጣ የህዝብ ቁጣ ከሚያመጣው ለውጥና ትርምስ ይልቅ ህዝቡ ይህን ትግል ተቀላቅሎ የአገራችንን አደገኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቀውስ ወደ ተረጋጋ ማረፊያ ይወስደዋል የሚል ፅኑ እምነት አለኝ።